በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ሰላማዊ ሰልፍ የተጠራው የጎፋ ክልል የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን የዘረኝነት መርዝ በማውገዝ ኢትዮጵያዊነትን አጉልቶና አሸብቆ ገለጸ።

ከቀመሩ ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአገሩና ለሕዝቡ ያለው ፍቅር፣ ኃላፊነትና ግደታ እጅግ ከፍተኛ የማይፈራና የማይታጠፍ ነው። በየትውልዱ አገሩን ከምንም ከማንም በላይ በማስቀደም ለመጠበቅ ኃላፊነትና ግደታን በመቀበል መስዋዕት የሚሆን የክፉ ቀን ሕዝብ ኢትዮጵያ አላት።

በመኢአድ ሰላማዊ ሰልፍ የተጠራው በደቡብ ኢትዮጵያ ሳውላ ወረዳ ጎፋ ክልል ማኅበረሰብ ያሳየው ኢትዮጵያዊነት እጅግ የላቀና የጎላ ከመሆን ጋር የወያኔን የዘረኝነት ክፋት፣አረመኔዊ መሰሪነት፣ጥፋትና ተንኰልን፣ፀረ_ ኢትዮጵያና ሕዝቧ፣ሃብቷን ዘረፋና የለም መሬቷን መሸጥ ተቃውሞ በማሰማት በመሪሪ አውግዘዋል።

የጎፋ ክልል ማኅበረሰብ ስሜቱንና ፍላጎቱን እጅግ ጥልቅና ከፍ አድርጐ የኢትዮጵያዊ ማንቱን ያሳየና ያንጸባረቀ፣ በአገራዊ አንድነትና ለአኩሪ ታሪካችን ያለውን ፍቅርና ክብር ያሳየበት በመሆኑ ለታሪካዊ ተግባሩ በቀዳሚ ምሳሌነት የሚጠቀስ ነው ብዬ የተሰማኝን ኩራትና አክብሮት በምስክርነት በዚህ ጹሁፌ አቀርባለሁ።

የጎፋ ክልል የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ የጠባብ ጎጠኝነት፣ አረመኔዊ ሥርዓትና አገር አጥፊነት የተሰቃዬና የተጐዳ፣ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን የተነፈገና ያጣ፣የተቆጣና የተበሳጨ የሳውላ ወረዳ ሕዝብ በህብረት በነቂስ ሁሉን አቀፍ ስላማዊ ሰልፍ በመውጣት በወያኔ እየተፈጸመበት ያለውን ግፍና ስቃይ በመቃወም ምሬቱንና እምቢታውን አሰምቷል።ይህ የጎፋ ማህበረሰብ በማበከር የጎጠኛው ወያኔን ወራሪነትና ፋሽስታዊ ድርጊቱ እንድያከትም ያስጠነቀቀ ያለመና ቆርጦ የተነሳ ትብብሩን፣ ቆራጥና የማይበገር ፣ እጅ የማይስጥ ብርቱና ጽኑ ሕዝብ ለመሆኑ በያዘውና ባሰማው መፈክር በተገቢ አሳይቷል። ኢትዮጵያዊ ፣ ለፀረ_ ኢትዮጵያ የማይሸሽ ኃይል መሆኑን እያስገነዘበ **"ኢትዮጵያዊነት የጐጠኝነት መርዝ ማርከሻ መድሃኒት ነው"** በማለት በመፈክሩ በጉልህ ያሳዬውና ደጋግሞ ከፍ በአለ ድምጽ በኩራትና በድፍረት በማሰማት የማንነትን ስሜት ገልጻል።

ከዚህም በመቀጠል የጎፋ ክልል ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብ በአንድ አሀዳዊ የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሕዝቧ ያመነ፣የጸናና የቆመ ጠባቂም ኃይል ለመሆኑ የገለጸበት መፈክር **"ሕዝባዊ አንድነታችን ለዘላለም ተጠብቆ ይኖራል"** ማለት ለአገሩ ያለውን ፍቅርና አለኝታ ይገልጻል። አገሩ ኢትዮጵያን፤ በወያኔ አጋሚዶ ለሁለት መከፈሏንና በቋንቋ ክልል መመደቧን አጥብቆ እየተቃውመና እያወገዘ፣ በኃይልና ተንኰል የተነጠቀውን የግዛት አንድነት፣የውሃ በርና ወደብ ኤርትራንና ቀይ ባህርን ፎርፌ እንዳልሰጠን የኛነቱን የሚያስገነዝብና የሚያሳስብ፣ የማይተወውም ለመሆኑ ሲያስገነዝ የኢትዮጵያን ምድራዊ ቅርጽና የግዛት አንድነት አቀማመጥና ክልል ማፒን በአረንጓዴ_ ቢጫ _ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ አስውበውና አሸብርቀው ከፍ አድርጐ በመያዝና በማሳየት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ተግባሩን በልዩ ኩራትና ተስፋ በተሞላበት ባህሪ በመግለጽ አሳስበዋል። ልብ ያለው ልብ ያድርግው።

ሰንደቅ ዓላማውን ያከበረና ጌጥ ያደረገ ይህ የጎፋ ሕዝብ የኢትዮጵያን ስንደቅ ዓላማ አረንጓዴ_ ቢጫ_ ቀዩን በእምነትና በድፍረት በአካሉ ላይ በማገልደም፣ በራሱና በአንገቱ ላይ በማድረግ፣ ከፍ አድርጐም በመያዝና በማውለብለብ የአንድ አገር፣ የአንድ ኢትዮጵያዊ ሕዝብ የነፃነት አርማውና መታወቂያ መለዮው እንደሆነች እምነቱንና ስሜቱን በኩራት አሳይቷል። ከዚህም ጋር በጀርመን ሬድው ቃለ መጠይቅ የተሰጠው አቋምና አስተያየት እጅግ ኢትዮጵያዊነትን የሚያኮራና ተስፍ ያለው የአገር አለኝታ የትግል ቀስቃሽ ወኔና ኃይል የአገርን ጉዳይ በተግባር ያመላከተ ነው ። የሚደነቅና የሚኮራበት ጀብዱ ሥራ ነው።

የሳውላ ወረዳ የጎፋ ክልል የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰልፉ ላይ ያሳውየው ማንነት፣አገሩን በጎጠኛ ባንዳዎች አስወርሮ በስቃይና በችግር፣በዝምታና በትዕግሥት ተገዥ ሆኖ እንደማይኖርና የእውነተኛ ኢትዮጵያዊም ባህሪና ወግም አይደለም ብሎ በጽኑ ያመነ ለመሆኑ በግልጽ በግንባሩ ላይ የሚታይ ነበር። ከዚህም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከማንም ከምንም በፊት የነፃነትና የዜግነት መብት መጠበቅ፣ ክብርና ኩራት፣ ታላቅነትና መታፈሪያም ነው ብሎ በእጅጉ እምነትና ተስፋ ያለው ፣ ታግሎም መብቱን ለማስከበር የቆረጠና የተነሳሳ ኢትዮጵዊ መንግሥትና የሕግ የበላይነትን የናፈቀ ስሜት በሰልፈኛው ሕዝብ ዓይን ላይ ከወኔው ድምጽ ጋር ይነበብና ያስተጋባ ነበር።

ሰለሆነም በዚህ የጎፋ ክልል ሕዝብ የታየው የህብረት ሰላማዊ ሰልፍ፣ያሰማው መፈክር፣ያሳዬው ኢትዮጵያዊ ስሜት፣ አሞተ ኮስታራ ወኔ፣የአገር ፍቅርና ክብር፣ አርቆ አስተዋይነት፣ያለመና ቆርጦ ለነፃነት በድፍረት መነሳሳት እጅግ የሚያኰራ፣ ተስፋ የሚጣልበትና ቀስቃሽ ኢትዮጵያዊ ባህሪ በመሆኑ በግሌ የተሰማኝን ኩራት እየገለጽሁ ለጎፋ ክልል ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ያለኝን አክብሮት፣ክብርና ፍቅር ስገልጽ በጥልቅ ልባዊ ደስታና ትትና ነው።የጎፋ ክልል ሕዝብ ያሳየው መነሳሳትና ኢትዮጵያዊነት ስሜት እጅግ የላቀ አገር አቀፍ የብሔራዊ ሰሜት በመሆኑ መላው የኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት አፍቃሪ ሕዝብ ሁሉ የሚኰራበትና አርአያ የሚያደርገው ነው። እንዲዚሁም በደሴ ከተማ የተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ፣ ኢትዮጵያ የሕዝቧ አገርነቷን ያረጋገጥና እንደ ቀደምት ትውልዳችን በጀግንት አገርን መጠበቅ እንዳለብን ያሳዬ ቀስቃሽና ተስፋ ያለው የቆራጥ እምነትና ተግባር በመሆኑ መጠቀስ ያለበት የሚከተሉት የትግል መስመርና አቅጣጫ ነው በማለት ለአገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ አገርህን አድን ጥሪን ጭምር አሳስባለሁ።

ሕዝብ የአገር ኃይልና ጠባቂ ነው !

ምንጊዜም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አሸናፊ ነው ! !

ባንዳ ይወድማል !